# ቤት ሲፈርስ !

በታሪክ ሠሪ ጀግኖች አጽም የተገነባ
በታላቅ መስዋዕት የደምቀለም የተቀባ
በጽኑ ግንብ የታነጸ ቤት ሲፈርስ
የፍራሹ ቡናኝ ለሁላችን ሲዳረስ
መጠለያ የለ ድንኳን ታዛ
ማንነታችን ለስደት ዓለም ሲገዛ
የፈረሰ ቤትን ማደስ ቀርቶ
ሁሉ የግል ጎጆውን መሥርቶ
እንዴት ነው ሀገርን ሀገር የምንላት ?
በቡድን እየተዳቆስንባት !!
በክርን እየተቧቀስንባት
የታለ የአንዲት ሀገር ባንዲራ ትርጉሟ
በሺ ቀለማት ተቀልማ
ምኑ ላይ ነው የአንድነት ምልክቷ ?
መታሰቢያቸው ሲሻር የጀግኖች የሰማዕቷ !!
ለብርቅዬዋ ኢትዮጵያና ለሰንደቅ አልነበር መድማታቸው
በነፍስ በአካል መስዋዕትነት መክፈላቸው ?
እነሱስ በክብር ወድቀዋል አንድ ጊዜ
ይብላኝ ለኛ ለተጠናወተን የሀገር ክኅደት አባዜ !!

ለማንኛውም ተከፋፈልን ! ተሰነጣጠቅን
የአንድነትና የዜግነት ራዕይ ጠፋብን !
በአምቻ ጋብቻ ወገን ለየን
በፖለቲካ ፓርቲና በዘር በነገድ ተለያየን
እንደ ሰው አስቦ መኖር ቢሳነን !
እንደ አራዊት በጥርሳችን ተነካከስን
ለተባበሩት ጅቦችም ራሳችንን አጋለጥን
ግን አሁንም ኢትዮጵያዊ ነን እንላለን
እንዲያው ለነገሩስ ማን ይሆን የረገመን ?

መርገምታችን ባመጣው ጣጣ
አንዳችን የአንዳችንን ዓይኖች ስናወጣ
ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል እንዲሉ
ጅቦቹ ተቃርበዋል እኛን ሊበሉ !!
ይኸው ተረባረቡብን
ፈጁን አፋጁን
በመጋዙ ጥርሳቸው ፈጩን
ለውቅያኖስ ጉሮሯቸው ዳረጉን !
ወገንም አስበልቶን ሊበላ
ከጅቦች ጋር ገብቶ መሃላ
እኛ ስናልቅ እሱም በተራው ሊተካ
ቀኑ የማይደርስ መስሎት ከጅቦች ጋር ሲያስካካ
እናት ኢትየጵያ ልትሆን የባዕዳን ፍሪዳ
በወገን ጠላት ስትነዳ !
አንድ አንበሳ ልጅ አጥታ
በሃፍረት አንገቷን ደፍታ !
ዕንባዋ የሁለት ዓይኖቿን ድንበር ጥሶ
ከጉንጮቿ ላይ ፈሶ !
በአንገቷ ሥር ወርዶ ደረቷን ገምሶ
ሁለመናዋን አርሶ
የአዳኝ ያለህ !
የልጅ ያለህ
ያገር ያለህ ብላ ስትጣራ
ሰሚ አጥታ በዝቶ ጣሯ
ያገር ያለህ ብላ ስትጮህ እማማ
ታዲያ ድምጽዋን ማን ሰማ ?
እምዬ እየተበላች ነው በቁሟ
ታዲያ ለማን ይሰማ ኅማሟ ?
ይኸው ዠንበር ልትጠልቅ በሁላችን
ፍም መስላ በላያችን
በአመለካከት ልዩነት ሳንግባባ
ሆነን መፍትሄ አልባ

አንድነት ሳይኖር አንድ መስለን
በፖለቲካ ቱማታ ራሳችንን አታለን
ይኸው ዠንበር እስክትጠልቅ እንጠብቃለን !!
እማማ ....የአዳኝ ያለህ
የሀገር ያለህ
የልጅ ያለህ ብላ ተጣርታ
የጣዕር ድምጽዋን አሰምታ
በአራቱም ማዕዘናት ጮሃ ሰሚ አጣች !!
ዋይ ዋይ ልጆቼን ብላ ደረቷን ደቃች !!
ስለ ልጆቿ አንድነት ማጣት አሰበች
ሆዷ ተንቦጫቦጨ አዘነች !
መቼም እናት ናትና ራራች
የሷ መከራ ኅማም መስሎ ሳይሰማት !
የኅፃንነት ወራታችን ትዝ ብሏት ተሣቃ
ወተት አልባ ጡቶቿን ሳታስበው ጨምቃ
በልጆቿ ርኅራኄ ቢስነት ተጨንቃ !
የአዳኝ ያለህ !
የሀገር ያለህ !
የልጅ ያለህ ብላ ጮኸች እማማ
ታዲያ ድምጽዋን ማን ሰማ ?
ዓይኖቿ  በዕንባ ተሞልተው ስታነባ
የገደል ማሚቶው ድምጽዋን ላገር ሲያስተጋባ
ዕንባዋ የዓይኖቿን ድንበር ጥሶ
ከጉንጮቿ ላይ ፈሶ
በአንገቷ ሥር ወርዶ ደረቷን ገምሶ
ሁለመናዋን አርሶ
እነሆ አሁንም ትጮሃለች
ሳትሰለች ጥሪዋን ታሰማለች
ከዕንባዋ ብዛት ውብ የነበረ ፊቷ ተጨማዶ
ኩራት ክብሯ ልዕልናዋ ተዋርዶ
የወላድ መሃን ስትመስል  እማማ
ታዲያ ማነው እሪታዋን የሚሰማ ?
ይኸኔ እናት ብትሆን ለልጆቿ
ደረቷን እየደቃች በእጆቿ
ወይ  እኔን አፈር ይብላኝ ሥቃያችሁን ልሠቃይ
ኅመም ሞታችሁን እንዳላይ
ብላ ታድን ነበር ልጆቿን
ታሪክ ይመሰክራል የእናትነት ሥራዎቿን !!
እኛስ ልጆቿ ምን ጎደለን ምን አነሰን ?
የእማማን ሥቃይ መስማት ለምን ተሣነን
እርስ-በርስ ከምናልቅ ተናክሰን
በአጉል ፖለቲከኛነት ስሜት ተቦጫጭቀን
ጥቅማችንን ለቀን ለጅቦች ሰጥተን
ጦም አዳሪነትን አስተናግደን
እስከመቼ የኋሊት እንጓዛለን ?
በቃ እንግዲህ ወገኔ ይብቃ
ያልነቃህ ንቃ
የነቃህ አንቃ
የናትህን ጥሪ ስማ
ሰባብረህ ጣለው የጠላትን አድማ
እናት ኢትዮጵያን አስከብር ከእሥራቷ ትፈታ
አንተም ባገርህ ተከበር የሤረኞችን ትጥቅ አስፈታ
ወገንህን ታደገው በሥቃይ ውስጥ ያለውን
በወኅኒ ቤት ታጉሮ  በስደት የሚማቅቀውን
በረንዳ አደሩን መከራ የጠበሰውን
በትግልህ አስወግድለት ሥቃዩን
ዠንበር ሳትጠልቅብን ጭለማው ሳይሸፍነን
በእናት ሀገራችን የነፃነት ብልጭታ ይታየን
ወገኔ ሕልመኛ ሳትሆን የተግባር ሰው ሁን
መከራህ ይብቃ ዛሬ ተላበሳት ነፃነትን
የተከበረው ቤት እንዳይፈርስ አስብ ሰማዕታትን
አስባት ኢትዮጵያ እናትን !!